ኤ.ሀ.ሠ.አ
የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ፡፡
Ethiopians' Citizen Democratic Union | Union Citoyenne Démocratique des Éthiopiens

www.slttunhzb.net
sh1@ttomar.net

ገ_ዐዓ_201801_ዐማርኛ

## የኢ.ሀ.ሠ.አ. ፡ የ 2018 ፡ ዓ.ም. ፡ መልካም ፡ ምኞት ፡ መልእክት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡—

# « ሊነጋ ፡ ሲል ፡ ይጨልማል ! »

ለንደን ፥ መስከረም ፡ 2018 ፡ ዓ.ም. ።

**የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ !**

እንኳን ፡ ለ 2018 ፡ ዓ.ም. ፡ በደኅና ፡ አደረሰኽ ፡ እያለ ፥ መጪው ፡ ዓመት ፡ የመሥዋዕትኽን ፡ ፍሬ ፡ የምታይበት ፡ ዓመት ፡ እንዲኾንልኽ ፡ ውጥን ፡ አካልኽ ፡ **የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት** ፡ ( **ኢ.ሀ.ሠ.አ.** ) ፡ ከልብ ፡ ይመኛል ።

**የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ !**

ነገር ፡ ኹሉ ፡ እልኩ ፡ ደርሷል ፤ የተፈጥሮ ፡ ሕግ ፡ ነውና ፥ ከልኩም ፡ አያልፍ ።

ግፈኞች ፡ እጆቹን ፡ እና ፡ እግሮቹን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምድር ፡ የምታያቸው ፡ ጥንተ ፡ ጠላትኽ ፡ ኢምፔሪያሊዝም ፥ ዛሬ ፥ ተራውን ፥ የፈተና ፡ ዘመንን ፡ ሊቀምስ ፡ ተቃርቦ ፡ ይታየናል ። ከንግዲህ ፡ ዘመኑ ፡ የፈጣን ፡ መሠረታዊ ፡ ለውጥ ፡ ነው ። የመገላገያውን ፡ ምዕራፍ ፡ ጨክኖ ፡ በአንድነት ፡ ታግሎ ፡ ከመሻገር ፡ ሌላ ፡ ማማረጫ ፡ የለምና ፥ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ የውንብድና ፡ አገዛዝን ፡ በማስወገድ ፥ ሀገራዊ ፡ እግዚእናኽ ፡ ወደሚከበርበት ፡ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ትግልኽን ፡ አጠናክረኽ ፡ ቀጥል ።

ኢ.ሀ.ሠ.አ. ፡ ያቀረበልኽ ፡—

"ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ሀገራዊ ፡ ቅያስ ።"

( www.slttunhzb.net )

እያደር ፡ የብዙኃኑን ፡ ድጋፍ ፡ እያገኘ ፡ ስለ ፡ ኼደ ፥ በ 2018 ፡ ዓ.ም. ፡ የመዠመሪያ ፡ ፍሬዎቹን ፡ ታያለኽ ፡ ሲል ፡ **ኢ.ሀ.ሠ.አ.** ፡ ሙሉ ፡ እምነቱን ፡ በድጋሚ ፡ ይገልጽልኻል ፨

ትሑት ፡ አገልጋይኽ ፡—

**ኢ.ሀ.ሠ.አ.**

እግዚእናችንን ፡ የማስከበር ፥

ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥

ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመመሥረት ፡

ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያ ፡ እና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡

**ለኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ እናብር!**

የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

# ሥልጡንሕዝብና ።

# www.slttunhzb.net